## 78 የአርማው አጠቃቀም

1. የኮሚሽኑ አርማ በፖሊስ መታወቂያ ካርድ ፣ በመለዮ፣በፖሊስ ተሽከርካሪዎች፣ ኮሚሽኑ በሚያመለክታቸው ሌሎች ስፍራዎች እና በሚወሰነው አኳኋን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል::
2. የኮሚሽኑ ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች እንደየስራቸው ጠባይ ከኮሚሽኑ አርማ በተጨማሪ የራሳቸው አርማ ሊኖራቸው ይችላል::
3. አርማው የሚይዛቸው የቀለም አይነቶች ፖሊስ በቀላሉ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲለይ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው :: የቀለም አይነቶቹ በመመሪያ ይወሰናሉ::
4.

## 79 ስለ መታወቂያ መለያ ቁጥር

1. ማንኛውም ፖሊስ: ፖሊስ መሆኑን የሚገልፅና በኮሚሽኑ የሚዘጋጅ የመታወቂያ ካርድ ይኖረዋል ::
2. የፖሊስ መታወቂያ ካርድ :-
   ሀ/ የክልሉን ፖሊስ አርማ
   ለ/ የፖሊሱን ሙሉ ስም : የስራ ደርጃ : የደም ዓይነትና መለያ ቁጥር ይይዛል :
3. ማንኛውም ፖሊስ ህግ ሲያስከብር የመታወቂያ ካርዱን ማሳየት ይኖርበታል::

## ክፍል አስራ ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 80. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

### 81 ተፈፃሚነት የሌላቸው ደንቦችና መመሪያዎች:

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያና የተለምዶ አሰራሮች ደንቡ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚነት የለውም::

### 82 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በሐረሬ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሐረር
ሚያዝያ 3 ቀን 1998 ዓ/ም
ሙራድ አብዱልሐዲ
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

ድሬ ማተሚያ ቤ.ማ.